# የበላይና የበታች የጦር መኮንን ግንኙነት

## የበላይ የጦር መኮንን

- ያዛል፣ መመሪያ ያወጣል፣ የክፍሉ ተግባራትን ያቅዳል፣ መርሃ-ግብር ያወጣል
- ለክፍሉ ስልጠና ትኩረት ይሰጣል
- በቅድሚያ ከክፍሉ ኦፐሬሽን፣ ስልጠናና የተያያዙ ጉዳዮችን ይሳተፋል
- በክፍሉ ብቃትና ዝግጁነት ትኩረት ያደርጋል
- የበታች መኮንን ስራውን እንዲወጣ ምቹ ሁናቴ ይፈጥራል
- የበታች መኮንንን ይረዳል

## የበታች ጦር መኮንን

- በትዕዛዝና በተሰጠው መመርያና እንዲሁም መርሃ-ግብር መሰረት የውሎውን ተግባራትን ይመራል፣ይፈፅማል
- ትኩረቱ በእያንዳንዱ ስልጠናና ባናሳው ክፍል የወል ስልጠና ይሆናል
- በቅድምያ በወታድሮች ስልጠናና፣ መሪነት እንዲሁም አናሳው የክፍል ጓድ በመምራት ተሳትፎ ያደርጋል
- እያንዳንዱ የበታች ጓድ፣ የበታች መኮንንና ወታደር በሚገባ ስራቸው ለመወጣት የተዘጋጁና እያንዳንዱ የጓድ አባል ተገቢ ስልጠና ያገኘ መሆኑን፣ እንዲሁም ወኔና ዝግጁነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል
- በበታች መኮንኖችና ተራ ወታደሮች አንድ ወጥ በሆኑ ተግባራት፣ ስልጠናና ሞያዊ ዕድገት ላይ ትኩረት ያደርጋል
- የመኮንኖችና የበታች መኮንኖች ትዕዛዝ ይከተላል

የበላይና የበታች መኮንኖች የጋራ ግብ አላቸው- የክፍሉ ተልዕኮ ማሳካት ነው። ሁለቱ መመካከር፣ መረዳዳትና አንዱ ካንዱ መማር አለባቸው

የበታች መኮንኖች ተራ ወታድሮችን ያስለጥናሉ፣ ይመራሉ እንዲሁም ይረዳሉ። ተልዕኮን ለማሳካት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ። ጥሩ ስነምግባርና ድስፐሊን እንዲሰፍንም ይጥራሉ። መኮንኖችና እንዲሁም አንዳንዴ ህዝብን ይወክላሉ።

## የበላይ አምሳ አለቃ ሻለቃ (ሲ ኤስ ኤም)

- የበታች መኮንኖች አለቃ ሻለቃ ጦርና ከዚያም በላይ ያዛል
- ያለው መርሃ-ግብር፣ የስራ ደንብ ስልጠናና ቁመና እንዲሁም ተግባራት በሚያዛቸው ወታድሮች ይተግብራል
- ላዛዥና ለአባላት ምክር ይሰጣል፣ እንዲሁም ሃሳብ ያመነጫል
- የክፍሉ የበታች መኮንኖች ሞያዊ ዕድገት መርሃ-ግብርን ያስተዳድራል
- በክፍሉ ዋና አሰልጣኝ ነው

- ቅድሚያ በሚሰጣቸው ተግባራትና ስልጠና እንዲሁም አስፈላጊ የበታች መኮንኖች ትምህርት ላይ ዋና አዛዡን በመርዳት ይሰራል
- ዋና አዛዡን በመወከል በወታድራዊና ህዝባዊ ጉዳዮች ይሳተፋል
- አዛዡን ዕቅድ በማቀድ፣ በማስተባበር፣ በማዋሃድ፣ ሁሉም ባንዴ-በማስኬድ ተልዕኮን ያሳካል፣ ይተባበራል

## የአምሳ አለቃ ሻለቃ (ኤስ ኤም)

- ከሻለቃ ጦርና ከዚያም በላይ ያሉትን አባላት ይቆጣጠራል
- የቴክኒክ ስራ የተካነበት ሞያው ነው
- የስራ ባለደረቦችን ዕቅድ በማቀድ፣ በማስተባበር፣ በማዋሃድና ባንዴ-በማስኬድ ተልዕኮን እንዲሳካና ሌሎች ተግባሮችም እንዲፈፀሙ ይተባበራል

## የመጀመርያ አምሳ አለቃ (ፈረስት ኤስ)

- በሻምበል ደረጃ አለቃ ነው
- ወታደርን ማሰልጠን ዋና ስራው ነው
- በክፍሉ በወታደሮችና ቤተሰቦቻቸውን ላይ የደህንነትና የጤናችው ጉዳይ ሃላፊነት አለበት
- ምክትል መቶ አለቃን ያሰለጥናል
- ባዛዡ የዕለት ስራዎች ላይ ይተባበራል
- የበታች መኮንኖችን ያሰለጥናል፣ ይረዳል
- አዛዡን ዕቅድ በማቀድ፣ በማስተባበር፣ በማዋሃድና ባንዴ-በማስኬድ ተልዕኮን እንዲሳካና ሌሎች ተግባሮችም እንዲፈፀሙ ይተባበራል

## አምሳ አለቃ (ኤም ኤስ)

- ከሻለቃ ጦርና ከዚያም በላይ ያሉትን አባላት ይገራል
- የቴክኒክ ስራ ሞያው ነው
- የስራ ባለደረቦችን ዕቅድ በማቀድ፣ በማስተባበር፣ በማዋሃድና ባንዴ-በማስኬድ ተልዕኮን በማሳካትና ሌሎች ተግባሮችም እንዲፈፀሙ ይተባበራል

## ምክትል መቶ አለቃ/ የመጀመርያ አምሳ አለቃ ደረጃ (ኤስ ኤፍ ሲ)

- ምክትል መቶ አለቃነት ግዳጅ እንጂ የወታደር መዓርግ አይደለም
- የዚሁ ግዳጅ መሪ ረዳትና አማካሪ ነው
- ወታደሮችን ማሰልጠንና በደህንነታችውን ላይ ሃላፊነት አለበት
- የዚሁ ግዳጅ ክፍል መሪ በማሰልጠን አዛዡን ይረዳል
- የግዳጁን አዛዥ ከሌለ እሱን በመተካት ይሰራል
- የወልና የግል ስራዎችን ያስተምራል

- የወታደሩን ደንብ መከበሩንና መጠበቁን ያረጋግጣል
- የግዳጁን መሪ ዕቅድ በማቀድ፣ በማስተባበር፣ በማዋሃድና የተዋሃዱትን ባንዴ-በማስኬድ ተልዕኮን በማሳካትና ሌሎች ተግባሮችም እንዲፈፀሙ ይረዳል

## የሰካድ፣ ክፍልና ጋድ መሪዎች (የስታፍ አምሳ አለቃ (ኤስ ኤስ ጂ)፣አምሳ አለቃ(ኤስ ጂ ቲ) ና አስር አለቃ(ሲ ፒ ኤል)

- በወታደሮችን ጤንነትና ደህንነት ላይ ሃላፊነት አለባቸው
- ወታደሮቹ ተገቢውን ቁመና አቋቋም መያዛቸውን ማረጋገጥና እንዲሁም ለግልና የክፍላቸው መሳሪያና ንብረት በሚገባ እንዲከባከቡ ያደርጋሉ
- አርአያ በመሆን ይመራሉ፣ ወታድሮችን ይዘው ግዳጅንምይመራሉ
- ደንቦችን በስራ ላይ ያውላሉ፡ እንዲሁም ወታድሮችን በወታድራዊ ሞያን እንዲሰለጥኑና እንዲሁም የክፍሉ ተልዕኮ እንዲሳካ ያበረታታሉ
- የነጠላና የጋራ ስልጠና ይሰጣሉ
- በባልደረቦቹ መሃከል ቅርርብን እንዲኖር ያደርጋሉ
- ጥሩ ባህርይና እሴት እንዲኖርም ያስተምራሉ
- ጥሩና በራስ የመተማመን መንፈስ ይገነባሉ
- ያስተባብራሉ፡ ያማክራሉ
- ውሳኔ መወሰን ያስተምራሉ፡ እንዲሁም የአካል ስልጠና ይሰጣሉ
- ያቅዳሉ፣ ያስተባብራሉ፣ እንዲሁም ተልዕኮንና ስራዎችን ይፈፅማሉ
- ወደ ሻለቃና ከዚያም በላይ ከሆነው አካል ማለትም ወደ የስታፍ አምሳ አለቃ፣ አምሳ አለቃና አስር አለቃ አካል ከተላኩ እዚያው ከተላኩበት ክፍል ባለው ወታድራዊ ዕውቀትና ደንብ መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ

---

* ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ወታድራዊ መዓርጎች ከኢትዮጵያ ወታድራዊ ማዕርግ የተለየ ነው። NCOs (Non-commissioned Officers) የሚባሉትን በኛ አጠራር የበታች መኮንኖች ተብለው ከሚጠሩት ጋር ይመሳሰላሉ